# መመሪያ ደንብ

MONTGOMERY COUNTY BOARD OF EDUCATION
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

ተዛማጅ/ተመሣሣይ ርዕሶች/ደንቦች: ACA, IGT-RA, JFA-RA, JHF-RA
ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፡- ዋና የአካደሚ መኰንን

## ጥቃት፣ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት

A. ዓላማ

ት/ቤቶች በጉልበት ከማጥቃት፣ ከዛቻ ወይም ከማስፈራራት ፀድተው አመቺና ሠላማዊ የትምህርት አካባቢ እንዲሆኑ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ቁርጠኛ ነው። ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ትምህርትን ይረብሽና በአካዴሚ ግኝት፣ ስሜታዊ ጤንነት፣ እና በት/ቤት አየር/ድባብ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያደርስ ይችላል።

በትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ፣ በት/ቤት አውቶቡስ ላይ፣ ወይም ት/ቤት ስፖንሰር በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ከማንኛውም ሰው በቃል፣ በአካል፣ ወይም በጽሑፍ (ኤሌክትሮኒክስ ጨምሮ) ማስጨነቅ፣ ጥቃት ወይም ማስፈራራት እንዳይኖር ለመከላከል የትምህርት ቦርድ ቁርጠኛ ነው።

ቦርዱ በተጨማሪ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ዘገባ በሚያቀርቡ ግለሰቦች ወይም በሚሸማቀቁ፣ በሚመሰክሩ፣ በሚታዘቡ፣ ወይም ስለ እንድ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ተግባር አስተማማኝ መረጃ ባለቸው ላይ በቀል ወይም ግብረመልስ ለመከልከል ግዴታ ገብቷል።

B. ጉዳይ

1. የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት መከላከል እንዲሁም የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ዘገባ በሚያቀርቡ ላይ በቀልን ለመከላከል ከተማሪዎች፣ አስተዳደር፣ እና የት/ቤት ሰራተኛ ጋር የመከላከልና ጣልቃ መግባት ስልጠና የሚያካትት ስርአት-አቀፍ ጥረት ይጠይቃል። የሚሸማቀቁ ተማሪዎች፣ እና ሌሎችን የሚያሸማቅቁ፣ የተለያዩ ትርጉም ያዘሉ የጤና፣ የደህንነት፣ እና የትምህርት አደጋ ተሞክሮዎች ሊደርሱባቸው ይችላል።

2. ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ እና በሜሪላንድ ህግ መሠረት ተሞርኩዞ፣ የሚከተሉት ትርጓሜዎች ይተገበራሉ፡-

    a) "ማጥቃት/ማስጨነቅ፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት" ማለት በቃል፣ በአካል፣ ወይም በጽሑፍ ሆንተብሎ የሚደረግ፣ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ሆንተብሎ በተማሪ የትምህርት ጥቅሞች ላይ፣ እድሎች፣ ወይም በአፈጻጸም ወይም በተማሪው(ዋ) የአካል ወይም ሳይኮሎጂያዊ ደህንነት እና ከፍተኛ በሆነ መልኩ ጣልቃ በመግባት የትምህርት የጥላቻ አካባቢን የሚፈጥር እና፡-

        (1) ወይም — በግለሰብ ትክክለኛ ወይም በይሆናል ግምት ባህርይ በመነሳሳት በቦርድ ፖሊሲ-Board Policy ACA ላይ እንደተገለጸው ከአድልዎ ነፃ የሆነ፣ ሚዛናዊነት/ፍትህ፣ እና የዳበረ ባህል፤ ወይም፣

            (a) ወሲባዊ ባህርይ ያለው፣ የተማሪን ሃፍረተ ገላ በመግለጽ ዓይነት ወይም የጽሑፍ/ሥዕላዊ መግለጫ ወይም በወሲባዊ ግንኙነት እንደተሳተፉ በማስመሰል አይነትን የሚያካትት፤ ወይም፣

(b) በዛቻ ወይም በማስፈራራት፤ እና፣

(2) ወይም ደግሞ—

(a) በት/ቤት ንብረት ውስጥ፣ በት/ቤት እንቅስቃሴ ወይም ክውነት፣ ወይም በት/ቤት አውቶቡስ ላይ የሚከሰት፤ ወይም፣

(b) ስርኣት የጠበቀ የት/ቤት ሥራ ክንውን በከፍተኛ ደረጃ የሚያሰናክል።

b) ሳይበርቡሊይንግ/Cyberbullying ማለት የማጥቃት/መጨቆን፣ ትንኮሳ/ጥቃት፣ እና የማስፈራራት አይነት ነዉ. "ሳይበርቡሊዪንግ" ማለት በኤሌክትሮኒክስ መሳርያ ኣማካይነት የሚተላለፍ መገናኛ ሲሆን በማህበራዊ ሚድያ ጣቢያዎች መገልገልንም ያካትታል። ሳይበርቡሊዪንግ በ"ኤሌክትሮኒክስ መገናኛ" ስር የሚውሉትን ማናቸውንም የወደፊት መተግበሪያዎች/applications ያካትታል።

c) "ኤሌክትሮኒክ መገናኛ/Electronic communication" ማለት በኤሌክትሮኒክ መሳርያ፣ ስልክ፣ ሞባይልን፣ ኮሚፒውተርን፣ ወይም ታብሌትን ጨምሮ የሚተላለፍ መገናኛ ማለት ነው።

d) ሃፍረተስጋ ብልቶች፣ በ Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-424፣ ላይ በተገለጸው መሠረት ራቁት አባለዘር/ሀፍረተ ስጋ፣ የሀፍረተ ስጋ/ብልት አካባቢ, ቂጥ, ወይም የሴት ጡት ጫፍ።

e) ወሲባዊ ግንኙነት፣ በ Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-424፣ ላይ እንደተገለጸው፣ ፍትወተ ስጋ መፈጸም ማለት፣ በሀፍረተስጋ-ለሀፍረተስጋ፣ በአፍ-ለሀፍረተስጋ፣ ቂጥ-ለሀፍረተስጋ፣ ወይም አፍ-ለቂጥ፣ በተመሣሣይ ጾታ ወይም በተቃራኒ ፆታዎች መካከል ነዉ።

በዚህ ፖሊሲ ላይ እንደተጠቀሰው፣ በጉልበት ማጥቃት በአካል ላይ ብቻ አያበቃም (ቡጢ መምታት/መጎንተል፣ መግፋት፣ መገፍተር)፣ በቃል (ማሾፍ-ማብሸቅ፣ ዛቻ/ማስፈራራት፣ ማስገደድ/በሃይል፣ ማሸሚጠጥ/መሳለቅ፣ የማዋረድ/የማንቋሸሽ ስሞችን መጥራት)፣ ወይም ተዛማጅ የሆኑ (ሃሜት መዝራት፣ ችላ ማለት ወይም ማግለልን) የሚያካትት ሲሆን በዚህ ብቻ አይወሰንም።

C. **አቋም**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራትን የመለየት ፕሮግራም ተግባራዊ ያደርጋል፤ ውጤታማ የሆኑ የመከላከያ ፕሮግራሞችን ይተገብራል ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ሲከሰቱ ጣልቃ ይገባል፤ የጣልቃገብነት ስልቶችን ይተገብራል፤ ካስፈለገም የውጭ መጣቀሻ/ማስተላለፍያም ያቀርባል። በት/ቤት ውስጥ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት፣ እና በማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ዘገባ በሚያቀርቡ ግለሰቦች ላይ በቀል ወይም ግብረመልስ መከልከል፣ እንዲሁም ውጤቶችና ማስተካከያ ተግባሮች/መፍትሄዎች የስርኣት-ኣቀፍ መከላከያና ጣልቃገብነት ፕሮግራም ኣካል ሆኖ መካተት ይኖርበታል። የዚህ ኣይነቱ ፕሮግራም ክፍለ-ኣካሎች የሚከተሉትን ማካተት ኣለባቸው፡-

1. መከላከል እና ጣልቃገብነት

a) ለአስተዳዳሪዎች እና ለሥራ ባልደረቦች ስለ ጥቃት፣ በዘር/በፆታ መተንኮስ (ማጥቃት) ወይም ማስፈራራት/ዛቻ መጠነ ሰፊነት፣ ምክንያቶችን፣ እና የሚያስከትለውን ውጤት ግንዛቤ ለማስጨበጥና በጥናት ላይ የተመሠረቱ ስልቶችን፣ የመፍትሔ እርምጃዎችን፣ እና ጥቃት፣

በዘር/በፆታ መተንኮስ (ማጥቃት) ወይም ማስፈራራት/ዛቻን መከላከል ሊያስከፍል የሚችለውን ውጤት ዓመታዊ የሙያ ማበልጸጊያ ግንዛቤ ለማሳደግ። ሞያዊ እድገት ለተሸማቀቁ ተማሪዎች፣ ላሸማቀቁ ተማሪዎች፣ እና ለዳር ቆሞ ተመልካች ተማሪዎች እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለበትም በተጨማሪ ማካተት አለበት።

b) በጉልበት ማጥቃት፣ የዘር/የፆታ ትንኮሳና ጥቃት፣ ወይም የማስገደድ የማስፈራራት ተግባርን የመከላከል ፕሮግራም ላይ የተማሪ ተሳትፎ የእኩያሞች/የጓደኛሞች ድጋፍ፣ መከባበር፣ ልዩነቶች እና ባህል ላይ ማስተዋል/ጥንቃቄ የሚያሻቸው የማጥቃት ሁኔታን ለአዋቂዎች/ለጎልማሶች ሪፖርት በማድረግ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማደፋፈር።

c) መጠነ ሰፊ ጥቃት፣ የፆታ/የዘር ትኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት/ዛቻ፣ ምክንያቶቹን፣ የሚያስከትለውን ውጤት ልጆቻቸውን የመርዳት/የመደገፍ ስልቶችን ለወላጅ/ለሞግዚት ለማሳወቅ ከቤተሰቦች እና ከማህበረሰብ ጋር ግንኙነት እና ተግባብቶ መሥራት።

d) ጥቃት፣ የፆታ/የዘር ትኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት/ዛቻ የህብረተሰብ ጤና ችግር በመሆኑ እና ጥቃት፣ የፆታ/የዘር ትኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት/ዛቻ የተፈጸመባቸውና ይህንን ጥፋት ለሚያደርጉ ተማሪዎችና ዳር ተመልካቾች ተማሪዎች ጭምር የጤና መገልገያዎች መኖራቸውን ለማሳወቅ ከማህበረሰብ የጤና እና የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ጋር መተባበር።

e) ጥቃት የተፈጸመባቸውን ተማሪዎች ደህንነት ማረጋገጥ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጥቃት፣ የፆታ/የዘር ትኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት/ዛቻን ለመከላከል የተለያየ ዓይነት ዘዴ/ስልት ዳብሯል።

2. የሚያስከትሏቸው መዘዞችና የመፍትሄ እርምጃዎች

የሚያስከትሏቸው መዘዞችና የመፍትሄ እርምጃዎች ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራትን ለፈፀሙ ግለሰቦች፤ በበቀል ወይም በግብረመልስ ላይ ለሚገኙ ግለሰቦች፤ እና ስለ ማሸማቀቅ ሃሰተኛ ክስ የመሰረቱ ግለሰቦች በፀናና በፍተሃዊ መንገድ በMCPS ደንብ JFA-RA፣ የተማሪ መብቶችና ሃላፊነቶች መሰረት መዳኘት አለባቸው።

3. የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ተግባሮች ዘገባ ኣቀራረብ ቅደም-ተከተሎች

a) ሥርዓቱ/(ሲስተሙ) ስለ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ተግባሮች ሪፖርት ለማድረግ፣ ለት/ቤቶች አመቺ የሆነ፣ ደህና፣ ግላዊ የሆነ እና ከእድሜ ጋር የሚመጥን አሠራር ቅደምተከተል ይሰጣቸዋል።

b) ስለ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ተግባሮች ሪፖርት ስለማድረግ አካሄዱን በእያንዳንዱ ት/ቤት ለተማሪዎች ሠራተኞች፣ እና ወላጆች/ሞግዚቶች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ቅጽ-MCPS Form 230-35 እንደሚገኝ ጭምር ይገልጽላቸዋል፣ስለ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ተግባሮች ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ።

c) በ MCPS ስለ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ተግባሮችን ሪፖርት ማድረግ የሚበረታታ እና የሚደገፍ ተግባር ነው። MCPS ዘገባ ማቅረብ/ማስታወቅ የሚሸማቀቁ ተማሪዎችን፣ የሚያሸማቅቁ ተማሪዎችን፣ እና ዳር ቆሞ ተመልካች ለሆኑ ተማሪዎች ለማገዝ እንደሚያመራ ግልፅ መልእክት ማስተላለፍ አለበት።

4. ስለ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ተግባሮችን ፈጣን ምርመራ የማድረግ ቅደም ተከተል።

a) ርእሰ መምህር ወይም ተወካይ ለሁሉም ወገን ስለ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ሪፖርት በሚመለከት ማስረጃ የማቅረብ እድል በመስጠት በፍጥነት ብቃት ያለው አስተማማኝ እና አድሎ የሌለበት ምርመራ ማካሄድ አለባቸው። ምርመራው እንደተጠናቀቀ፣ ርእሰ መምህር ወይም ተወካዩ የመፍትሔ እርምጃዎችን እና ያስከተለውን መዘዝ እንደየአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ እና የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ሁኔታ ዳግመኛ እንዳይከሰት የመከላከል ደረጃዎችን መተግበር ወይም ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት የተፈጸመበት/የተፈፀመባት ተማሪ እና ሌሎችም ላይ አስፈላጊ ከሆነ አድሎአዊነት ያስከተለውን ተጽእኖ ማረም አለበት/አለባት።

b) የት/ቤት አስተዳዳሪዎች በጥቃት ተግባር ክስተት ለተሳተፉት ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች በፍጥነት ማሳወቅ አለባቸው።

c) ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የሥራ ባልደረቦች/አባላት የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ሁኔታ ቀጥሎ እንደሆነ ለማጣራት ጥቃት ከደረሰበ(ባ)ት ተማሪ እና ጥቃት ከፈጸመው/ከፈጸመችው ተማሪ ጋር ግላዊ እና የግል ኮንፈረንሶችን ያካሄዳሉ።

5. ለተጠቂ ተማሪ፣ ለአጥቂ ተማሪ፣ እና ለዳር ቆሞ ተመልካቾች የሚቀርቡ የድጋፍ አገልግሎቶች

አንድ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት አድራጎትን በማስመልከት ከሰራተኛ አባል ጋር ለመወያየት አንድ ተማሪ ምኞቱ/ቷን ከገለፀ/ች፣ የሰራተኛው አባል ተማሪው/ዋን ተግባራዊ በሆነ፣ ደህና/አስተማማኝ፣ ግላዊ፣ እና ከእድሜ-ጋር-አግባብ ባለው መንገድ ለመተግበር ጥረት ያደርጋል።

ስርአቱ ለተማሪዎችና ለቤተሰቦች የሚጠቁ ተማሪዎች፣ የሚያጠቁ ተማሪዎች እና ዳርቁሞ ተመልካች የሆኑ ተማሪዎች በት/ቤቶቹና በማህበረሰቦቹ በሁለቱ ውስጥ ሊያገኟቸው የሚችሉ አገልግሎቶች ዝርዝር በቅርብ እንደሚያገኟቸው ያደርጋሉ።

## D. ተፈላጊው ውጤት

ከማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ነፃ የሆነ ትምህርታዊ አካባቢ ለመፍጠር ት/ቤቶች የመከላከያና የጣልቃገብነት ስልቶች፣ እንዲሁም ውጤቶችና ድጋፎች ያቀርባሉ።

## E. የአተገባበር ስልቶች

1. የት/ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ ይህንን ፖሊሲ ለመተግበር፣ በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ ሠራተኛ በ MCPS ዉስጥ ስለ ጥቃት፣ ዛቻ እና ማስፈራራት የሪፖርት አቀራረብና ምርመራ ሂደት ቅደምተከተል ልምድ ያለው(ያላት)፣ እንደአስፈላጊነቱ ለወላጆች/ለሞግዚቶች እና ለህግ አስከባሪዎች የማሳወቅ፤ጥቃት የተፈጸመበት/የተፀመባት ተማሪ እና ጥቃት ያደረሰ(ች)ው ተማሪ እንዲሁም ለዳር ቆሞ ተመልካቾችም፣ ድጋፍ የመስጠትና መዘዙ የሚያስከትለውን የመፍትሔ እርምጃዎችን ትግበራ ህግ የማስፈጸም እና እንዴት እንደተከሰተ መረጃ የመቆጣጠር /የመከታተል፣ ልምድ ያለው(ያላት) የሚመለከተው ሠራተኛ ስም የሚገልጽ መመሪያ ያዘጋጃል።

2. የት/ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ በጉልበት ማጥቃትን፣ የጾታ/የዘር ጥቃትና ትንኮሳን፣ ወይም ማስፈራራት/ማስገደድን በት/ቤቶች ውስጥ ለመከላከል ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የትምህርትና የሙያ ማበልጸጊያ ፕሮግራሞችን ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች።

3. ቦርዱ ያፀደቃቸውን ፖሊሲዎች ለማስፈጸም የሚዘጋጁ መመሪያዎች በሙሉ እንደ መደበኛ የኢንፎርሜሽን/የመረጃ ልውውጥ አካል ለቦርድ ይላካሉ።

F. **ግምገማ-ክትትል እና ሪፖርት**

ይህ ደንብ በቦርድ ድህረ እይታ ሂደት መመርያ መሰረት ይገመገማል።

ተዛማጅ ምንጭ:- Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-303.1, §7-424, §7424.1

**የፖሊሲው ታሪክ:-**አዲስ ፖሊሲ በውሳኔ ቁጥር 132-10 መሰረት፣ማርች 9/2010 ፀደቀ፤ በውሳኔ ቁጥር 489-16 መሰረት፣ ኖቨምበር 15/2016 ተሻሻለ፤ ቴክኒካል ማሻሻያ በውሳኔ ቁጥር 319-17፣ ጁን 26/2017፤ቴክኒካል ማሻሻያ በውሳኔ ቁጥር 351-18፣ ጁን 25/2018.